# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 178 ጥቅምት 2 2004 ገጽ 1


በመለስ ዜናዊ እና ዘረኛ ቡድኑ ዙሪያ ያሉ ሰዎች ሁሉ የመለስን አገዛዝ ከልባቸው ይደግፋሉ ብሎ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አያምንም። አንዳንዱ በአንድ አጋጣሚ ገብቶ መውጫ ቀዳዳ አጥቶ የሚዳክር ነው። ሌላው ደግሞ ባለሙያ ነኝ፤ የሙያ አገልግሎት ብቻ እየሰጠሁ ነው እያለ እራሱን የሚያታልል ነው። ቀሪው ደግሞ "ወይን-ለኑሮ" በተሰኘው ዘይቤ "ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" እያለ ለጊዜዓዊ ጥቅም ሲል የተጠጋ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ ሶሪያዊያንን ሲሰልል የተገኘ አሜሪካዊዉ የሶሪያ ዜጋ ክስ ተመሰረተበት

በስደተኛነት ገብቶ የአሜሪካ ዜግነት የተሰጠዉና አብረዉት በዩናይትድ ስቴትስ ነዋሪ የሆኑ የሶሪያ ዜጎች የአገራቸዉ መንግስት በወገኖቻቸዉ ላይ የሚያደርሰዉን የሰብአዊ መብት ረገጣ በመቃወም የሚያደርጉትን ሰላማዊ ሰልፍ በተለያየ መልክ እየመዘገበና እየቀረፀ ለሶሪያ መንግስት በድብቅ መረጃ ሲያቀብል የተገኘ ሶሪያዊ ክስ የተመሰረተበት መሆኑን አሶስየትድ ፕሬስ ዘግቧል።

መሃመድ አናስ ሃታም ስኡድ የተባለዉ ቅጥረኛ የራሱን ወገኖች በመሰለል መረጃዉን ለሶሪያ መንግስት እንደሚሰጥና በየጊዜዉ ወዳገሩ እየተጓዘ ከፕሬዝዳንት አሳድና ከሌሎች ባለስልጣናት ጋር እንደሚገናኝ ታዉቋል።

በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኘዉ የሶሪያ ኤምባሲ "መሰረትና ተቀባይነት የሌለዉ" በማለት ክሱን አጣጥሎታል። እንደተባበሩት መንግስታት ድርጅት ግምት ከ3 ሺህ ያላነሱ ሰላማዊ ዜጎችን የገደለዉ የአሳድ አምባገነን መንግስት ድምበር በመሻገር በዉጭ አገር የሚገኙ የዳያስፖራ አባላት አረመኔያዊ ተግባሩን እንዳይቃወሙ ሰላዮችን ማሰማራቱ የህዝብን የለዉጥ ጥያቄ በሃይል ለማፈን የሚያደርገዉን ጥረት ያሳያል ተብሏል።

አክቶበር 3 ቀን የወጣዉ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ዘገባ የሶሪያ መንግስት ኤምባሲዎችና ሌሎች ቅጥረኞቹ በዉጭ አገር የሚገኙ ሶሪያዊያንን እንደሚያሳድዱ መግለፁ የሚታወስ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ የብሪታኒያ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በአገሩ የሚገኙትን የሶሪያ አምባሳደር ጠርቶ በብሪታኒያ የሚገኙ ሶሪያዊያንን አንድ ዲፕሎማት ለማስፈራራት ጥረት ማድረጉን በመግለፅ አነጋግሯቸዋል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በአነስተኛ ጥቅማጥቅም በመደለል የወያኔ አገዛዝ ካድሬ ለመሆን የተዳረጉ ወጣቶች የወያኔውን ኢሃዴግ ፍጹም ህሊና ቢስነት በመገንዘብ ላይ ነን አሉ

በአዲስ አበባ ከተማ የተደራጁ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ዘርፍ ታዳሚ የሆኑ አያሌ ወጣቶች "የፖለቲካው መሣሪያ ሊያደርገን ያሰባሰበን ኢሕአዴግ ፍጹም ህሊና-ቢስ እና ከማህበረሱቡ ጋር ማንኛውም ዓይነት ግንኙነት የሌለን ፍጡራን አድርጎ በመቁጠር እራሱ የፈጠረውን ችግር ህብረተሰቡን እያወናበድን እንድንቀርፍለት ጫና እየፈጠረብን ይገኛል" ማለታቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

ኢሳት በሪፖርቱ እንደገለጻው መስከረም 30 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀትር በኋላ ለዘጋቢያችን አስተያየታቸውን የሰጡትና ምሬታቸውን የገለጹት በአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንዱስትሪ የተደራጁ ወጣቶች "ሽረሪት አንድ ግዜ ነው የምታደራው ፤ድሯም የሚያገለግለው ለአንድ ግዜ ነው፤ እኛ ግን ሰዎች በመሆናችን እንደሽረሪት ልንሆን አንችልም፡፡ከዚህ በፊት አማራጭ አጥተንም ሆነ ተወናብደን አንድ ግዜ የኢሕአዴግን የፖለቲካ ድር በሕዝብ ላይ ለማድራት ሞክረናል፡፡ ዳግመኛ ግን አይቻለንም፡፡ የህብረተሰቡ ልጆች በመሆናችን ቤተሰቦቻችን የሚገጥማቸውን ዘርፈ-ብዙ ችግር የምናውቅና የምንጋራም ነን" ካሉ በሁዋላ "የወያኔው ኢሕአዴግ ቅጥፍት ላይታረም ከራሳችን ህሊና እና ሁሉን እያወቀ የኢሕአዴግን ውሸት ስንግተው ከሚታዘበን ህብረተሰብ ጋር የምንጋጨው ለምንድን ነው?" ሲሉ ይጠይቃሉ ብሉአል።

ወጣቶቹ አክለውም "የሰሞኑ ስብሰባ እና ጉዳያችንን ተወጡልን የሚለው ኢሕአዴጋዊ ውትወታ ሰልችቶናል፡፡ ሌላው ቀርቶ እኛ ከዚህ ቀደም ለተደራጀንበት የሥራ ዘርፍ ችግር ማስወገጃ አቅርበንለት ለነበረው አንድ ሺ አንድ ጥያቄዎች ለአንዱም እንኳን መልስ መስጠት ያልሆነለት ሥርዓቱ ከእንግዲህ ከኛ ጋር ተፋቷል፣ ከሕዝቡ ጋር እንደተፋታ ሁሉ..." ማለታቸውን ኢሳት ገልጹአል፡፡

የወያኔው ኢህአዴግ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአባላቱ ከፍተኛ ጥያቄ እየተነሳበት በመምጣቱ ግምሽ የሚሆኑት አባላቱን ለማባረር መወሰኑን በተደጋጋሚ የተገለጸ ሲሆን በሰሜን ሸዋ የሚገኙ የኢህአዴግ መምህራን አባላት ራሳቸውን ከአባልነት ማግለላቸውንና ስብሰባዎችንም አንካፈልም ማለታቸውን ቀደም ብለን መዘገባችን ይታወሳል።

የግንቦት7 ንቅናቄ በያዝነው ሳምንት ለንባብ ባበቃው ርእሰ አንቀጹ የወያኔው ኢህአዴግ አባላት ጊዜው ሳይረፍድ መስመራቸውን እንዲያስተካክሉ ጥሪ ማድረጉ ይታወሳል።

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ዓለም አቀፉ የገንዘብና የልማት ተቋአም አይ ኤም ኤፍ የኢትዮጵያ የገንዘብ ፖሊሲ በጣም ምስቅልቅሉ የወጣ ነው በማለት አጣጣለው

በያዝነው ጥቅምት ወር ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በይፋ ያመነው መረጃ እንደሚያመለክተው በሃገሪቱ እየታየ ያለው የገንዘብ ግሽበት መጠን አሁንም እያሻቀበ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የምግብ ሸቀጦች ዋጋም እየናረ መሆኑ ታወቀ። ይሄው ሪፖርት እንደአመለከተው የገንዘብ ግሽበት መጠን ከ 40.1 በመቶ በላይ ሲሆን በምግብ ዋጋዎች ላይ ያለው የግሽበት መጠን ደግሞ 51 በመቶ መድረሱ ታውቁአል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፈው መስከረም ወር የነበረው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ የ25 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱ ተጠቅሶአል።

የዋጋ ግሽበቱን በተለያዩ ክልሎች በመከፋፈል ያወጣው ይሄው ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ እጅግ ከፍተኛው የዋጋ ግሽበት የታየው በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል እስከ 60 በመቶ በመድረስ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የደቡብ ክልል፣ የጋምቤላ፣ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልሎች የከፍተኛ ዋጋ ግሽበት ሰለባዎች መሆናቸው ታውቁአል። በአንጻሩ ዝቅተኛ ግሽበት ተከስቶባቸዋል የተባሉት ክልሎች ደግሞ አዲስ አበባ ድሬ ዳዋና የትግራይ ክልል መሆናቸውም ታውቁአል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዓለም አቀፉ የገንዘብና የልማት ተቋአም በያዝነው ወር ባወጣው ሪፖርት የኢትዮጵያ የአምስት አመት እቅድ የተጋነነና ውጤታማ ለመሆኑም የሚያጠራጥር መሆኑን የገለጸ ሲሆን የዓለም ባንክም ተመሳሳይ የሆነ ሪፖርት አውጥቱአል።

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋአም አይ ኤም ኤፍና ወርልድ ባንክ የዘጋቢዎቻቸውን ጥናት ዋቢ በማድረግ እንደገለጹት ኢትዮጵያ እየተከተለች ባለው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የአምስት አመት የትራንስፎርሜሽን እቅድ አስፈላጊውን መስፈርት ያላሙዋላ ነው ብለውታል።

የአምስት አመቱ የልማት ግቦች የተጋነኑና ሊሳኩ አይችሉም የሚሉባቸውን ነጥቦች የገንዘብ ተቋማቱ ዘርዝረው ያቀረቡ ሲሆን የዘራፊው መለስ መንግስት እየተከተለ ያለው ገንዘብን የመርጨት ፖሊሲ የገንዘብ ግሽበት በማስከተሉ፣ አደጋው በመጪዎቹ አምስት አመታት በተመሳሳይ ሁኔታ ሊቀጥል ይችላል ብለዋል።

በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ዙሪያ ያሉ በርካታ ማነቆዎችን የዘረዘሩት አይኤም ኤፍና የወርልድ ባንክ አጥኝዎች የወያኔው አገዛዝ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ጣልቃ ገብነት ቀንሶ የንግዱ ማህበረሰብ በስፋት እንዲሳተፉበት እንዲያደርግ መክሯል። ሙስና ሌላው ችግር መሆኑን የጠቀሱት ተቋማቱ ዘረኛው አገዛዝ ሙስናን ለመከላከል አቅጃለሁ ቢልም የመተግበሪያ መንገዱን ግን አላስቀመጠም ብለዋአል።

የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ አገኘሁት ለሚለው የኢኮኖሚ እድገት ሁሌም የአለማቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችን በዋቢነት እንደሚጠቅስ የሚታወቅ ቢሆንም ቀደም ብሎ አይ ኤም ኤፍ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚና ገንዘብ ፖሊሲ ላይ ይፋ ያደረገው አሉታዊ ሪፖርት የዘራፊዉን አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ እጂግ አበሳጭቶ እንደነበር አይዘነጋም።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የተከሰተውን የርሃብ አደጋ ስፋትና ጥልቀት ለመሸፋፈን ቢሞክርም ችግሩ ከቁጥጥር ያለፈ በመሆኑ ገሃድ እየወጣ መሆኑ ተገለጸ

በምስራቅ አፍሪቃ በተለይም በኢትዮጵያ የተከሰተውን የርሃብ አደጋና እልቂት ጨካኙና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የማለባበስና የመደበቅ ሙከራ ቢያደርግም የርሃብ አደጋው ስፋትና ጥልቀት ከዘረኛው አገዛዝ የመደበቅ ሙከራ የላቀ በመሆኑ ችግሩ ለአለም ህዝብ ይፋ እየሆነ መምጣቱ ታወቀ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የተከሰተው ረሃብ ለበርካታ ዜጎች እልቂት ምክንያት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይሄው ርሃብ በተከሰተበት አካባቢ ባሉት አዋሳኝ ክልሎችም የተከሰተው ድርቅ በተጨማሪ የዝናብ እጥረት መባባሱ ታውቁአል። ለተለያዩ ተግባራት ወደ ደቡብ የኢትዮጵያ ክልል የተጉአዙ የአይን እማኞች ለተለያዩ ዜና አውታሮች እንደገለጹት በደቡብ ክልል በየሜዳውና አስፋልት ዳርቻ የተለያዩ የቤት እንስሣት አልቀው እንደሚታዩና በርካታ ከብቶቻቸው የሚሞቱባቸው አርብቶ አደሮች ሳር ፍለጋ ከሞት የተረፉትን ለማዳን እየገሰገሰገሱ፤ እንደሚገኙ ታውቁአል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የቪ ኦ ኤ ዘጋቢ እንደገለጸው ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል 705ኛው ኪሎሜትር በቦረና ዞን የሚታየውን ድርቅና ከፍተኛ የሆነ የእንስሳት ሞት በግልጽ ያሳያል ያለ ሲሆን ከ1.5 ኪሎሜትር እስከ 2 የሚሆን ርቀት ውስጥ 16 የሞቱ የከብት ቅሪቶችን ቆጥረናል፣ ይሄ በመንገዱ ዳር ያየነው ብቻ ነው። ውስጣ ውስጡን ያለቀውን፣ ወድቆ የሚታየውን የእንስሳት ቅሪት አድማስ ይቁጠረው በማለት ገልጾታል።

እንደ ቪ ኦ ኤ ዘጋቢ ሪፖርት የሚበዛው ነዋሪ ከከብት እርባታ በሚገኙ ተዋጽዖዎች የሚተዳደርበት ቦረና ከ60-75 ከመቶ የሚሆኑ ከብቶች መሞታቸው እንደሚገመት ገልጾ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንደሚለው ከሆነ የሚያዝያው ወር የገና ዝናብ ለሁለተኛ ጊዜ ሳይጥል በመቅረቱ ከሩብ ሚሊዮን በላይ ከብቶች ሞተዋል ማለቱ ታውቁአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጥሪ በመለስ ዜናዊ ጎራ ለሚገኙ ወገኖቻችን

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በከፍተኛ ሽብር ውስጥ ገብቷል። ይህ አገዛዝ የቆመበት መሠረት በጣም ስስና ደካማ በመሆኑ በዘወትር ስጋት ውስጥ ነው።

በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ለመለስ ዜናዊ የወገኑ ኢትዮጵያዊያን መኖራቸው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሌለው ጥንካሬ ያለው እንዲመስል አድርጓል። ይህ ደግሞ በተራው የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊያንን መከራ አብዝቷል።

በመለስ ዜናዊ እና ዘረኛ ቡድኑ ዙሪያ ያሉ ሰዎች ሁሉ የመለስን አገዛዝ ከልባቸው ይደግፋሉ ብሎ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አያምንም። አንዳንዱ በአንድ አጋጣሚ ገብቶ መውጫ ቀዳዳ አጥቶ የሚዳክር ነው። ሌላው ደግሞ ባለሙያ ነኝ፤ የሙያ አገልግሎት ብቻ እየሰጠሁ ነው እያለ እራሱን የሚያታልል ነው። ቀሪው ደግሞ "ወይን-ለኑሮ" በተሰኘው ዘይቤ "ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" እያለ ለጊዜዓዊ ጥቅም ሲል የተጠጋ ነው።

ይሁን እንጂ ደጋግመን ልናስታውሰው የሚገባ ሃቅ አለ። በማንኛውም ምክንያት ከመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ጎን የቆመ ኢትዮጵያዊ አገሩን ኢትዮጵያንና ወገኖቹን እየጎዳ ነው።

ዛሬ ያሉ የኢህአዴግ ድርጅቶች በሙሉ የመለስ ዜናዊ የስለላ ተቋማት ናቸው። ለህወሃት ፍቅር ያላችሁ ወገኖች ስሙ! ያ የምትወዱት ህወሃት ዛሬ የለም። ዛሬ ያለው የመለስ ዜናዊና የአዜብ መስፍን የግል የስለላ ተቋም ብቻ ነው። የዛሬው ህወሃት ለትግራይ ልጆችም አይተኛም። ለብአዴን መልካም አመለካከት ያላችሁ ወገኖችም ስሙ! ብአዴን ዛሬ የለም። ዛሬ ያለው የመለስ ዜናዊና የአዜብ መስፍን የግል የስለላ ተቋም ብቻ ነው። ብአዴን ለአማራ ልጆችም አይተኛም። በሌሎችም የመለስ ዜናዊ አሻጉሊት ድርጅቶች ውስጥ ያላችው ኢትዮጵያዊያን ንቁ!!! ድርጅት የሚባል ነገር የላችሁም። ድርጅት የሚመስሉት ነገሮች የመለስ ዜናዊና የአዜብ መስፍን የግል የስለላ ተቋማት ብቻ ናቸው። በተቋማቱ መሣሪያነት፤ በእናንተ ተባባሪነት ወገን ሲበደል፤ አገር ስትፈራርስ ማየት እንደምን ያስችላችኋል?

"ቤተሰብ አለኝ፤ ልጆች አሉኝ" የሚሉ ሰበቦች የመለስ ዜናዊ ቡድንን ለመጠጋት ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ልጆችም ቢሆኑ የሚመኩበት አባት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ።

በትንሹም ቢሆን ከመለስ ቡድን ጋር መነካካት ለመለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ የልብ ልብ መስጠት ነው። በትንሹ እንኳን የጥቅም ተካፋይ የሆነ ሰው ትልቁን ዘረፋ የመቃወም የሞራል ብቃት አይኖረውም። በዚህ የተበረታታው የመለስ ዜናዊ ቡድን እነሆ ዛሬ የእርሻ መሬቶችን ለባእዳን ቱጃሮች እስከ መሸጥ ደርሷል። ይህን እየታዘቡ ከመለስ ዜናዊ ጋር መተባበር እንደምን ይቻላል?

በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፍርሃት በፈጠረው የወያኔ ጨካኝነትና ድድብና ተጠቅተዋል። ሰላማዊ ዜጎች "ሽብርተኛ" እየተሰኙ ብልቶቻቸውን ሳይቀር ተቀጥጠዋል። የመለስ ዜናዊ ቡድን ፈሪነት "ጀሮ ጠቢነትንና" ወሬ አቀባይነትን ተሰምቶ ወደ ማይታወቅበት ደረጃ አሳድጎታል። ይህ ደግሞ በሕብረተሰባችን ውስጥ የነበረውን እና ለዘላቂ አብሮነታችን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ማኅበራዊ መተማመንን እያጠፋው ነው። ይህን እያዩ ከመለስ ዜናዊ ጋር እንዴት መተባበር ይቻላል?

ደግመን እንለዋለን። የመለስ ዜናዊ ቡድን ደካማና በዘወትር ስጋት ውስጥ ያለ ነው። የሌለውን አቅም የሰጡት በተለያዩ ምክንያቶች ከጎኑ የቆሙ ኢትዮጵያዊያን ናቸው።

የዛሬ ጥሪያችን ለእነሱ ነው!

ወገኖች!

የመለስ ቡድን በኢትዮጵያ ጥላቻ የተሞሉ፤ የግል ጥቅም ያወራቸው፤ ትዕቢተኞች፣ ማይማን፣ ጉረኞችና ዘረኖች ስብስብ ነው። እነሱ የተካኑት ራሳቸው ያጠመዱትን ፈንጂ በቪዲዮ እየተቀረጹ ማምከንን ነው። እነሱ የተካኑት ሽብር በመንዛት ህዝብን በፍርሃት ቆፈን አስሮ መግዛትና ሃብቱን መቦጥቦጥ ነው። ፍርሃትን ማንገስ የተለመደ የአምባገነኖች የመጨቆኛ መሣሪያ ነው። ፍርሃት ለተወሰነ ጊዜ ዜጎች ተዋርደው፣ ተረግጠውና ተቀጥቅጠው እንዲገዙ የማድረግ አቅም አለው። ሆኖም ግን ፍርሃት ያቆመው ሥርዓት ለመናድ ጊዜ አይፈጅበትም። ፍርሃት ያቆመው የበርሊን ግንብ በሰዓታት ፈርሷል። በፍርሃት የቆሙ የቤን ዓሊ፣ የሙባረክና የጋዳፊ መንግሥታት ፈራርሰዋል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ውድቀትም ተመሳሳይ እንደሚሆን ጥርጥር የለንም።

እናም በመለስ ዜናዊ ጎራ ያላችሁ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መስመራችሁን አስተካክሉ። ነገ ሊረፍድባችሁ ይችላል። በአገራችሁ፤ በወንድሞቻችሁና በእህቶቻችሁ ላይ ብዙ ውድመት ከደረሰና ብዙ ጥፋት ከተሰራ በኋላ "መስመራችንን አስተካክለናል" ከተጠያቂነት አታመልጡም።

አንዳንዶቻችሁ ከዚህ በፊት ላቀረብናቸው ጥሪ አዎንታዊ መልስ ሰጥታችኋል። ይህ መልካም ነገር ነው። ከፊሎቻችሁ ግን ለመወሰን እንደተቸገራችሁ እንሰማለን። እናንተን የምንጠብቅበት ጊዜ የለንም። የቆማችሁበትን መስመር በፍጥነት ፈትሻችሁ አስተካክሉ።

ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ራሳችሁን ለማግለል የወሰናችሁ ወገኖቻችን፣ የአገዛዙን እድሜ ለማሳጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ በማድረግ እስከዛሬ - በማወቅም ሆነ ባለማወቅ - የበደላችሁትን ህዝብ እንድትክሱ እንጠይቃለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

## በኖርዎይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የፋሽስቱን መለስ ዜናዊ ጉብኝት በመቃወም የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ

በእንግሊዝኛ አጠራሩ "Energy for All" ማለትም ሃይል ለሁሉም በሚል መርህ በኖርዎይ ሃገር ኦስሎ ከተማ ላይ በተካሄደ ባለው ዓለም አቀፍ ስብሰባ ንግግር ለማድረግ የተጋበዘው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ፤ በኖርዎይና አካባቢዋ ከሚገኙ አጎራባች ሃገራት የተሰባሰቡ ኢትዮጵያዊያን ባደረጉት ከፍተኛ የሆነ የተቃውሞ ሰልፍ ምክንያት ተሸማቆና አንገቱን ደፍቶ ወደስብሰባ አዳራሽ እንዲገባና እንዲወጣ መገደዱን ዘጋቢያችን ከኖርዎይ ኦስሎ ከተማ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

በትናንትናው እለት በተካሄደው በዚሁ ስብሰባ እንዲገኝ የተጋበዘውን ዘረኛና አምባገነን ቁንጮ መለስ ዜናዊ ለመቃወም ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን የተገኙ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ በኦስሎ ከተማ በእለቱ የነበረውን ከፍተኛ ቅዝቃዜ በመቋቋም የተቃውሞ ሰልፉን ያካሄዱት ኢትዩኦጵያዊያን እልህና ቁጣ በተሞላበት መንፈስ በርካታ መፈክሮችን እያስተጋቡና የተቃውሞ ድምጻቸውንም ሲያሰሙ መዋላቸውን ዘጋቢያችን ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተቺሏል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ተቃውሞውን ለማሰማት የተሰባሰበው ህዝብ የፋሽስቱ መለስ ዜናዊን ወደስብሰባ አዳራሽ ማምራት በርቀት በተመለከተ ጊዜ ቁጣው ፈንቅሎት ለሰልፍ የተፈቀደለትን ቦታ ጢሶ አንገቱን ለማነቅ በሆይታ በመነጎዱ ሥነሥር ዓት ለማስከበር በቦታው ከነበሩት የኖርዌዬ ፖሊሶች ጋር መጋጨቱን በዚህም የተነሳ ሶስት ኢትዮጵያዊያንን ለተወሰኑ ሰአታት ታስረው መለቀቃቸው ታውቆአል።

መለስ ዜናዊ በህዝባችንና በአገራችን ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃና ወንጀል ለማውገዝ የወጣው ሰልፈኛ ካሰማቸው መፈክሮች መካከል መለስ ዜናዊ ሽብርተኛ ነው መለስ ዜናዊ ዘረኛ ነው፣ መለስ ዜናዊ ነፍሴ ገዳይ ነው፣ መለስን ወደ ኖርዎይ ሳይሆን ወደ ሄግ ለፍርድ ላኩት፣ ዘረኛው መለስ ለፍርድ ከቀረበልን ወደሃገራችን ለመመለስ ዝግጁ ነን፣ ኖርዎይ መለስ ዜናዊን መጋበዟና ማስተናገዷ ውርደት ነው፣ በሽብርተኝነት ስም በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የጅምላ እስራት ይቁም፣ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ ይፈቱ፣ መለስ ዜናዊ አሁኑኑ ይወገድ፣ መለስ ዜናዊና አገዛዙ አሸባሪዎች ናቸው፣ የኖርዎይ መንግስት ለኢትዮጵያው አሸባሪ አገዛዝ የሚያደርገውን እገዛና ድጋፍ ያቁም የሚሉና ሌሎች መፈክሮች ይገኙበታል።

በኦስሎ ከተማ በተካሄደው በዚሁ ሰልፍ ኢትዮጵያዊያኑ የፖለቲካ የትግል መስመርና ዘር ሳይለያቸው በአንድነት ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ እንደነበር የገለጸው ዘጋቢያችን፣ በእለቱ የተቃውሞ ሰልፍ የኦሮሞ ነጻነት ግምባር፣ የኦጋዴን ነጻነት ግምባር፣ እንዲሁም የተለያዩ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጂቶች አባላት በጋራ ሆነው ተቃዉሞአችውን ሲያሰሙ ውለዋል።

## ዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ የስዊድን ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ የታሰሩ ባልደረቦቻቸዉን ክስ በኢትዮጵያ ተገኝተዉ እንዳይከታተሉ ከለከለ

አፋኙና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ሽብርተኞች ናቿሁ በማለት ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞችን አስሮ እንደሚገኝ የሚታወስ ሲሆን የጋዜጠኞቹን የፍርድ ቤት ክስ ሂደት ለመከታተል ጥያቄ ያቀረቡትን የታሳሪ ጋዜጠኛ ባልደረቦች የወያኔው አገዛዝ ወደ ኢትዮጵያ እንደይገቡ መከልከሉ ታወቀ።

የሁለቱ ታሳሪ ጋዜጠኞች ማለትም ማርቲን ሺቤይ እና ጆሃን ፐርሰን ክስ የሚሰማዉ በመጪዉ ሳምንት ዉስጥ ኦክቶበር 18 ቀን መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ በችሎት ላይ ለመገኘት ቪዛ የጠየቁ የስዊድን የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች እስካሁን ወደ ኢትዮጵያ የመግቢያ ፈቃድ እንዳልተሰጣቸዉ ለማወቅ ተችሏል።

ሽብርተኞች ናችሁ በመባል ከታሰሩት ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞች አንዱ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ዉስጥ ታስሮ እንደነበር ዘረኛው መለስ ለኖርዌይ የዜና አገልግሎት የገለጸ ቢሆንም የስዊድን ጋዜጠኞች ቃል አቀባይ የመለስ አባባል ትክክል እንዳልሆነ ተናግሩአል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በስዊድን የሚገኙ ጋዜጠኞች በስቶክሆልም የክሮኖ-በርግ እስር ቤት ዙሪያ በመገኘትና እጆቻቸዉን በማስተሳሰር የስዊድን መንግስት በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እጂ ለወደቁት ለእስረኞቹ ትኩረት ይሰጥ ዘንድ ተቃዉሟቸዉን በሰላማዊ ሰልፍ ገልፀዋል። ይህ ጋዜጠኞቹ የጀመሩት የተቃዉሞ ሰልፉ ሁለቱ ጋዜጠኞች ፍርድ ቤት እስኪቀርቡ ድረስ እንደሚቀጥል ለማወቅ ተችሏል።

ኦላ ላርስሞ የተባሉት የስዊድን የፀሃፊዎች ማህበር ሊቀመንበር፤ " የስዊድን ጋዜጠኞች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ካልተፈቀደላቸዉ በጋዜጠኞቹ ላይ ምን ሊደርስ እንደሚችል አናዉቅም" በማለት ስጋታቸዉን ተናግረዋል።

ባለፈዉ አርብ በጉተንበርግ እና በስቶክሆልም የስዊድን ጋዜጠኞች በተመሳሳይ ሁኔታ መንግስት እስረኞቹን እንዲረዳ የጠየቁ ሲሆን የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ እና ጠ/ ሚኒስትሩ መንግስታቸዉ አስፈላጊዉ ሁሉ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ መናገራቸውም ታውቁአል።

ሁለቱ ስዊድናዊያን ጋዜጠኞች ከኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አዉጪ ግንባር አማፅያን ጋር ከተያዙበት ከጁላይ አንድ ቀን ጀምሮ በእስር ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል።

አሸባሪው የወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሽብርተኝነት ታፔላን በመለጠፍ በርካታ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራር አካላትንና አክቲቪስቶችን እንዲሁም በርካታ ጋዜጠኞችን ወደ እስር ቤት ማጎሩ ይታወቃል።

## በተቃወምከው ግዜ ቀንበሩን ከላይህ ላይ ትሰብራለህ!!

ላለፉት ሃያ ዓመታት በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ የተጫነብን ቀንበር መከራችንን አብዝቷል። መከራውም መሸከም ከምንችለው በላይ በመሆኑ ሮሮአችን ገደቡን ጥሶ ሦስት ትውልድን በአንድ ላይ እያስለቀሰ ነው። ህጻናት ልጆች ደጋግ አባቶቻቸው በካቴና ታስረው ወደ ወይኒ ሲጨመሩ እያዩ አምርረው እያለቀሱ ነው።የሚንከባከባቸው ውድ አባታቸው ለምን እንዲህ በአደባባይ ተይዞ እንደሚታሰር የሚነግራቸው ባለመገኘቱ ለጋ አእምሯቸው ለጭንቀት ተጋልጧል። የቤቱ ምሰሶ አባት በመታሰሩ ምክንያት እናቶች ልጆቻቸውን የሚመግቡትን ማቅረብ ባለመቻላቸው በጎስቋላ ቤታቸው ጣሪያ ሥር እያለቀሱ ነው። እንባቸው በፈርኦን እጅ ስቃዩዋ በዝቶ እንዳለቀሰችው ራሄል እንባ ጽዋውን ሞልቶ እየፈሰሰ ነው።

ዛሬ በአገራችን ሰውንም የማያፍር እግዚአብሄርንም የማይፈራ መለስ ዜናዊ የሚባል ሌላ ፈርኦን ተነስቷል። ይህ ሌባና ክፉ ዘረኛ ግለሰብ  የዜጎችን በህይወት የመኖርና ያለመኖር እድል ፈንታ ወሳኝ ሁኗል።

የፈርኦን እጅ በድሆች ዜጎች ላይ በጠነከረ ግዜ የፈጣሪን ፊት እስከሚያይ ድረስ ክብርን ያገኘ አንድ ሰው ተነሳ። ሙሴ ይባላል። ሙሴን የመሰለ ነብይም ዳግም አይነሳም ተብሎ በመጽሃፍ ቅዱስ ተጽፎ እናነባለን።

ሙሴ የፈጣሪን ፊት እስከሚያይ ድረስ ያደረሰው ምንድ ነው ?

ሙሴ በፈርኦን ቤት ያደገ የንጉስ ልጅ ልጅ ተብሎ በድሎትና በምቾት ይኖር ነበር። ፈርኦን ደግሞ ሰውንም ያማያፍር እግዚአብሄርንም የማይፈራ ክፉ ሰው ነበር። በዚህ ክፉ ፍጡር ቤት ውስጥ በድሎትና በምቾት ከመኖር ይልቅ ወገኖቹ  የተሸከሙትን የመከራ ቀንበርን መቃወም በመምረጡ የፈጣሪን ፊት እስከሚያይ ድረስ ደረሰ።

ዛሬ ብዙዎች በመለስ ዜናዊ ማእድ ዙሪያ ተሰባስበው  ጮማ እየቆረጡ ባለ ቀለሞችን መጠጦች እየተጎነጩ በደስታና በድሎት ሠክረዋል። ሚሊዮኖች በችጋር ሲያልቁ የዘመኑ ፈርኦኖች ግን በድሆች ላይ እየተሳለቁ ነው።

ለራሳችሁ ክብር የምትሰጡ ኢትዮጵያዊያን በተቃወማችሁት ግዜ ቀንበሩን ከራሳችሁ ላይ ትሰብራላችሁና ሳታፈገፍጉ የዘመኑን ፈርኦናዊያን በእውነትና በጽናት ተቃወሟቸው።

የዘመኑ ፈርኦኖች 8.5 ቢሊዮን ሰርቀው በውጭ አገራት ባንኮች ሲያስቀምጡ ኢትዮጵያዊያን በራብና በበሽታ ይቀጣሉ። መለስና ግብረ-አበሮቹ ልጆቻቸውን በአውሮፓና በአሜሪካን ልከው እንደላቀው ሲያስተምሩና ሲያኖሩ ኢትዮጵያና ልጆቿ ግን ከቀያቸን ዘልቀን እንዳናልፍ ተደርገን ዘመኑ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ ተለይተንና ርቀን እንድንኖር ተፈርዶብናል። ይህን የመሰለ ግፍ በገዛ አገራችን ላይ ሲፈጸም ዝም ለማለት ሰው መሆናችን ያስገድደናል።

ከዚህ ሁሉ ውረደትና እንግልት በኋላ የሚያስፈራን ምንድ ነው? ሞት ነው? አሁንስ ቢሆን  ኢትዮጵያና ልጆቿ ከሞት መች አመለጥን? መለስ ዜናዊ በፈለገና ደስ ባለው ግዜ ዜጎችን ገድሎ ቤተሰቦቻቸውን ሜዳ ላይ ላለመበተኑ ምን ዋስትና አለን? መለስ ዜናዊ የጫነብን የመከራ ቀንበር ዛሬ ካልተቃወምነው ነገ ሸክሙ በልጅ ልጆቻችን ላይ የከፋ ትውልዱንም መለስ ዜናዊ ለሚፈጥረው ክፉ ዘረኛ ሥርዓት ትተን እንድናልፍ ይሆናል። ልጅ ልጆቻችንም በገዛ አገራቸው መጻተኛና ስደተኞች ሁነው ይኖራሉ።

መለስ ዜናዊ በሃሰት ዜጎችን እየከሰሰ የሞትና የእድሜ ልክ እስራት ሲፈርድ አይተን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማን መሆን ፈጣሪን እፈራለሁ ከሚል ሰው የሚጠበቅ ተግባር አይደለም። ፍትህ ሲጓደል ህግ ለመለስ ዜናዊ ቂም መወጣጫ ሲሆን እያየን እስከ መቼ  ዝም እንላለን? በመለስ ዜናዊ ዘረኛና ዘራፊ ስርዓት የብዙ ደጋግ ዜጎች ቤተሰቦች ሜዳ ላይ ተበትነው ጦማቸውን ሲያድሩ እያዩ ዝም ማለት ትክክለኛ ተግባር አይደለም። እንዲህ ዓይነቱን ግፍ ተሸክመን እንኖር ዘንድ አይገባም። መለስ ዜናዊን የመሰለ ዘረኛና የሌቦች አለቃ ክብራችንን ሲያዋርደውና የመኖር ህልውናችንን ሲፈታተነው እያየን ዝም ለማለት አኛ ሆዳችን የሚገዛን አይደለንም። ማንነታችንን ለዘመኑ ፈርኦኖች አሳልፈን ለመስጠት ሃሞታችን አይፈቅድም። ሰው ከመሆን ተራ ሊያወጣን የሚሰራውን ዘረኛውንና ዘራፊውን ሥርዓት በቻልነው መንገድ ሁሉ እንታገለዋለን። ለክብራችንም ስንል ከተገፉ ወገኖቻችን ጎን ቆመን አገራችንን ከሌቦች እናጸዳለን።

በመጨረሻም ክብርህን የምትወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ማወቅ ያለብህ ማንም ሰው ሊረዳህ አይመጣም። ሳታፈገፍግና ሳታቅማማ የተጫነብህን ቀንበር ለመስበር መቃወም ያንተና ያንተ ድርሻ ብቻ ነው። ታላቁ ነብይ ሙሴ ፈርኦን በወገኖቹ ላይ የጫነውን ቀንበር በመቃወሙ ፈጣሪ አክብሮታል።አንተንም ፈጣሪ ያከብርህ ዘንድ የጨለማውን ጣኦት መለስ ዜናዊን በቃህ ማለት ከአንድ ፈጣሪን እፈራለሁ ከሚል ሰው የሚጠበቅ የተወደደ ተግባር ነውና ለጨለማው ጣኦት እምቢ በማለት ክብርህን ማስጠበቅ አለብህ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን !!!**

## ወያኔ ህዝብ ከፋፍሎ ለመግዛት ባለው ራዕይ የፈጠረው የሃይማኖት አክራሪነት ከፍተኛ የሆነ የደህንነት ስጋት ማስከተሉን  ባለሥልጣናቱ ገለጹ

በአገራችን ውስጥ ለዘመናት የኖረውን የባህል፤ የቋንቋና የሃይማኖት ልዩነቶችን ለሥልጣን እድሜ ማራዘሚያ እንደ አይነተኛ መሳሪያ ሲጠቀምበት የኖረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ አንዱን እምነት ተከታይ በሌላው ላይ በጠላትነት ለማስነሳት ሲያደርገው የነበረው የውስጥ ለውስጥ ሥራ አደባባይ ላይ መታየት በመጀመሩ "የአገሪቱን ደህንነት ሊያሰጋ ከሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሶአል" በማለት ህዝብ ለማሸበር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲ አበባ በላከልን ሪፖርት ገለጸ።

ለዘመናት በሰላም ተከባብሮና ተቻችሎ የኖሩትን የሁለቱን ታላላቅ ሃይማኖቶች አባቶችን ለፖለቲካ ሥርዓቱ ታማኝ በሆኑ ግለሰቦች በመተካት፤ የአንዱ ዕመነት ተከታይ ሌላውን በጥርጣሬና በጥላቻ እንዲመለከት ላለፉት 20 አመታት ያልተቋረጠ መሰሪ ሥራ እንዲያከናውኑ ሲያደርጋቸው ከቆየ ቦኋላ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ አክራሪዎች ተነስተዋል፤ ሰላምና ጸጥታ ሊያደፈርሱ ነው ወዘተ በሚል ሰበብ መግለጫ እንዲሰጡ እያደረጋቸው መሆኑ ታውቆአል።

በዚሁ መሰረት ሰሞኑን የእምነት ዳይሬክተር ጄኔራል የተባለው መረሳ ረዳ "የዋህቢዝም እምነት ተከታዮች በህቡእ በመንቀሳቀስ አመጽ እየቀሰቀሱና እረብሻ እንዲፈጠር እየሰሩ ነው" በማለት ለጋዜጠኞች መግለጫ መስጠቱ ታውቆአል። መግለጫውን ተከትሎም የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር የሆነው ሽፈራው ተክለማርያም ይህንኑ ወያኔ ራሱ የፈጠረውን የውሸት ስጋት በመድገም "የዋህቢ እምነት ተከታዮች ራሳቸውን በህእቡ በማደራጀት ከፍተኛ የሆነ የጸጥታ ስጋት ደቅነዋል" በማለት አስተጋብቶአል።

በወያነ የፌደራል ፖሊስ ዋና ጽህፈት ቤት ውስጥ ሰሞኑን በተካሄደው የግንዛቤ ማሸጨበጫ ጉባኤ ተብዬ ስብሰባ ላይ የወያኔ ባለሥልጣናትና የመንፈስ አባቶች ተብዬዎች ከዚህ ቀደም በተከታታይ በሀረር፣ በጂማ፣ በወለጋ፣ በኢሉባቦርና በባሌ  የታዩት ግጭቶች በሙሉ የዋህቢ እምነት አክራሪዎች የፈጠሩት ነው ማለታቸው ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል። ከዚህም አልፈው ዋህቢዎች ኢትዮጵያን በሼሪያ ህግ የምትተዳደር የሙስሊም አገር ለማድረግ እየሰሩ ናቸው ማለታቸው ለዘመናት ተከባብሮና ተቻችሎ በሰላም የሚኖረው ክርስቲያኑንና ሙስሊሙ ህብረተሰብ በጥርጣሬ እንዲተያይና በኑሮ ውድነትና በአስተዳደር በደል ምክንያት በወያኔ ላይ አንድ እየሆነ የመጣውን የተቃውሞ ድምጽ ለመከፋፈል አልመው መነሳታቸውን  ለሁለቱም እምነቶች ቅርበት ያላቸው ሰዎች ይናገራሉ።

የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች ወያኔ አንድ ጊዜ የሙስሊሙ ሌላ ጊዜ ደግሞ የክርስቲያኑ ደጋፊ አድርጎ ራሱን በማቅረብ፣ ለዘመናት ታችቸሎ የኖረውን ህዝብ በማበጣበጥ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እየሞከረ ነው ማለታቸውን ዘግቦአል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወያኔ  አህባሽ የሚባለው የእስልምና እምነት እንዲስፋፋ በፖሊሲ ደረጃ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ በርካታ ሙስሊሞችን እያስቆጣ ነው ተብሎአል፡፡

በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ጉዳዮች ሁሪያ ጸሀፊና ተመራማሪ የሆኑት አቶ አቡበክር አለሙ ሰሞኑን በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ "የዚህ ሰሞኑ የኢህአዴግ ሀይማኖተኛነት እንቆቅልሽ" በሚል ርእስ ባወጡት ጽሁፍ የአዲስ አበባ የፍትህ ቢሮ ሀላፊ አቶ ጸጋየ ሀይለማርያም ለሙስሊሞች በተዘጋጀ ስብሰባ ላይ "ቅንጅትና ኢህአዴግ አንድ ላይ ሊደራጁ እንደማይችሉት ሁሉ ውሀብያና ሱኒም አንድ ላይ ሊሆኑ አይችሉም" በማለት የተናገሩትን  ነቅፈዋል።

አደስ ዘመን ጋዜጣም መስከረም 19 2004 ዓ.ም. በእኩልነት ከማያምኑ ጸረ ሰላም ሀይሎች ሙስሊሙ ህብረተሰብ ትክክለኛውንና ከአያት ቅድመ አያቶቹ የተረከበውን የእስልምና እምነት እንዲጠብቅ፣ እምነቱን ለመከለስ ከሚንቀሳቀሱ አክራሪዎችና ጽንፈኞች እራሱን እንዲያገልና የጸረ ሰላም ሀይሎች ድብቅ አላማ ማስፈጸሚያ እንዳይሆን ማስጠንቁን ጸሀፊው ገልጸዋል።

አቶ አቡበክር በጽሁፋቸው "ለመሆኑ ህብረተሰቡ ከአያት ቅድመ አያቶቹ የተረከበውን ነገረ ሀይማኖት የትኛው እንደሆነና  በጸረ ሰላም ሀይሎች የተበረዘውን እና የተከለሰውን የሀይማኖት ቀኖና ደግሞ የትኛው እንደሆነ እንዲያውቅና እንዲገነዘብ የማድረግ ሀላፊነት ያለበት ማነው? መንግስት ወይስ የሀይማኖቱ ሊቃውንት?" ሲሉ ጠይቀዋል።

ከወራት በፊት በወሎ ዩኒቨርስቲ የሚማሩ 6 የዩኒቨርስቲ ሴት ተማሪዎች አክራሪ የሆነውን እስልምና ትከተላለችሁ በሚል በፌደራል ፖሊሶች ተይዘው ማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ መታሰራቸውን የግንቦት 7 ድምጽ ዘግቦ እንደነበር ይታወሳል።

## በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ ሶሪያዊያንን ሲሰልል የተገኘ አሜሪካዊዉ የሶሪያ ዜጋ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የፌዴራል አቃቢያን ድርጊቱ የአሜሪካንን የህዝቦች የመሰብሰብ ህገ መንግስታዊ መብት የሚፃረርና ተቀባይነት የሌለዉ እንደሆነ ገልፀዋል። የዩናይትድ ስቴትስ የምስራቅ ቨርጂኒያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ማክ ብራይድ "መሰብሰብና በሰላማዊ ሰልፍ ተቃዉሞ ማቅረብ በአሜሪካ ምድር ላይ መብት በመሆኑ ይህንን መብት ሰዎች እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ማንም ሰዉ ማስፈራራት አይችልም" ብለዋል።

የአሜሪካ የብሄራዊ ፀጥታ ቃል አቀባይ ቶሚ ቪተር በበኩላቸዉ "ይህ በዩናይትድ ስቴትስ ተቃዋሚ ሰላማዊ ሰልፈኞችን ለመቆጣጠር የአሳድ መንግስት የሚያደርገዉ ቁጥጥር የጭካኔ ተግባሩ እንደይጋለጥ ለማፈን ማንኛዉንም ነገር እንደሚፈፅም ያሳያል" በማለት ገልፀዉታል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሽብርተኛው መለስ ዜናዊ ባቋቋመው የዲያስፖራ ጽቤት አማካይነት በውጪ ያሰማራቸው ሰላዮች ተመሳሳይ እጣ እንደሚገጥማቸው አንዳንድ መረጃዎች ለኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን መድረሱን ኢሳት ዘግቦአል። በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የወያኔን ነፍሰገዳይ አገዛዝ እድሜ ለማራዘም እርዳታ የሚሰጡትንና በስለላ ስራ ላይ የተሰማሩትን ባንዶች ዝርዝር በተጨባጭ ማስረጃ በማስደገፍ መረጃውን ለዝግጅት ክፍላችን በስልክ ወይም በኢሜል  በማስተላለፍ እንዲተባበሩ የግንቦት 7 ድምጽ ጥሪውን ያቀርባል።

## “ኢትዮጵያ ባለፉት 20 የወያኔ አገዛዝ አመታት ከ አሥራ አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚበልጥ ገንዘብ ተዘርፋለች” ሲሉ በአለም ባንክ ለረጅም አመታት የሰሩ እንድ ታዋቂ የምጣኔ ሃብት ምሁር ገለጹ

ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ጀምሮ በኢትዮጵያ ስም በልማት እርዳታና በብድር ከአለም አቀፍ ህበረተሰብ ካገኘው መጠነ ሰፊ ገንዘብ ውስጥ ከአስራ አንድ ቢሊዮን በላይይ የሆነ ገንዘብ በባለስልጣናቱ መዘረፉን በአለም ባንክ ለረጅም ጊዜ ያገለገሉና በኢትዮጵያ ምጣኔ ሃብት ላይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱት ታዋቂው ኢኮኖሚስት ዶ/ር አክሎግ ቢራራ ገለጹ።

ዶ/ር አክሎግ ቢራራ ይህን የገለጹት ባለፈው እሁድ መስከረም 28 ቀን አዲስ አበባ ከሚገኙ በርካታ የአንድነት ደጋፊዎች ጋር በስካይፒ ባካሄዱት ውይይት መሆኑን የኢትዮጵያ ሳታላይት ድርጅት ኢሳት ገለጸ።

እንደ ኢሳት ዘገባ ዶ/ር አክሎግ በኢኮኖሚው ዙሪያ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ችግር ነው ያሏቸው፤ የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ግሽበት፣ የወጣቶች ሥራ አጥነት፣ የሀገሪቱ ሀብት በጥቂቶች መያዝና ሥር የሰደደ ሙስና ናቸው::

በዚህም ምክንያት የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በጥናት ላይ የተመረኮዘ ማስረጃ በመስጠት መንግስት ፖሊሲዎቹንና አካሄዱን እንዲያስተካክል በተደጋጋሚ ቢመከሩም፤ ሰሚ ባለመኖሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ ችግሮቹ እየሰፉ መሄዳቸውን አመልክተዋል ተብሎአል።

ዶ/ር አክሎግ ጥናቶችን ዋቢ አድርገው እንደገለፁት ”በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ 90 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ሲሆን፤ ከነ'ኚህ መሃል 7 በመቶ የሚሆኑት ህፃናት፤ ወላጅ አልባ ናቸው:: 46 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፤ በአሁኑ ሰዓት አገሩን ጥሎ ለመሰደድ እንደሚፈልግ ጥናቶች ያረጋግጣሉ” ብለዋል ዶ/ር አክሎግ።

ባለፉት 20 የወያኔ አገዛዝ አመታት ለአገሪቷ ከለጋሾች በብድርና በእርዳታ ከተሰጠው ገንዘብ ውስጥ ከ11 ቢሊዮን ዶላር በላይ በባለሥልጣኖች እንደተወሰደ መረጃዎችን ተንተርሰው አመላክተዋል። ዶ/ር አክሎግ እንዳሉት፤ በደርግ መንግስት ዘመን ኢትዮጵያ በ17 ዓመታት ውስጥ ያገኘችው ጠቅላላ ብድርና እርዳታ 4 ቢሊዮን ዶላር ያህል ሲሆን፤ በወያኔ አገዛዝ ዘመን ግን እስከ 40 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል ብለዋል።

ከዚህም ገንዘብ ውስጥ ያለፉትን ሶስት ዓመታት ሳይጨምር 8.4 ቢሊዮን ዶላር በህገወጥ መንገድ በኢትዮጵያ በባለሥልጣኖች አማካኝነት ወደውጭ መወሰዱን የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራምን ጥናት ዋቢ በማድረግ አውስተዋል።

አጠቃላይ በ20ው ዓመታት በህገ-ወጥ መንገድ በባለስልጣናት ተወስዶ በውጪ ባንኮች ተቀምጦ የሚገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ ገንዘብ ግን፤ ከ 11 ቢሊዮን ዶላር በላይ መድረሱን ነው የገለፁት። ይህም የሚያሳየው፤ በአገሪቱ ሙስና እጅግ መንሰራፋቱን ነው ብለዋል የኢኮኖሚ ባለሙያው።

ዶ/ር አክሎግ አክለውም ”ህዝቡ የተዘረፈውን ከ11 ቢሊዮን ዶላር የሚበልጥ ገንዘብ ለማስመለስ አሁን መጨነቅ የለበትም። መቅደም ያለበት ነገር፤ ገዥውን ፓርቲ ከሥልጣን ማውረድ ነው። ከዚያም ልክ እንደ ቱኒዚያ፣ ግብጽና ሊቢያ መሪዎች ገንዘቡን ለማስመለስ በውጪ የምንገኝ አገርና ወገን ወዳድ ዜጎች ጥረት እናደርጋለን። ለዚህ አቅሙም፤ ዝግጁነቱም አለን” ብለዋል።

ዶ/ር አክሎግ በገለፃቸው ማጠቃለያ ህዝቡ ትግሉን አጠናክሮ እንዲቀጥል በአፅንኦት በመግለፅ፤ እርሳቸውም አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

“ግመል የሚያሻግሩትን መርቆ እየሸኘ፤ መርፌ በሚወስዱት ላይ ይበረታል” የሚባለው የኢትዮጵያ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፤ ባለፉት አስር ዓመታት ለፍርድ ቤት ባቀረባቸው ከ500 በላይ ክሶች፤ አንድንም የመንግስት ባለስልጣን ለመክሰስ እንዳልደፈረ ማስረጃዎች ያመለክታሉ።

ኮሚሽኑ በቅርቡ 10ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ሲያከብር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥናት ያቀረቡት ምሁር ”ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የመንግስት ተሿሚዎችን ይፈራል”ማለታቸው ይታወሳል።

ፀረ-ሙስና ኮሚሽኑ መቋቋሙን ተከትሎ ዝርፊያው ተባብሷል የሚሉ ውስጥ አዋቂዎች ደግሞ፤ የቀበሌ ገንዘብ ያጉዋችን እንዲቀጣ የተቋቋመ የሚመስለው ይህ ኮሚሽን- ይህችን ድሀ አገር እንኳን ከሙስና ሊታደጋት ቀርቶ ይባሱኑ ለታላቅ ዝርፊያዎች ሽፋን በመስጠትና ሙስናን በማስፋፋት የአገሪቱን ድህነት እያባባሰ ነው በማለት ሲከሱ ይደመጣሉ።

## ኤርትራዊ ዲፕሎማትን በማጉላላት የህወሃት አገዛዝ የፀጥታ ሃይሎች ወንጀል መፈፀማቸዉን አንድ የኤርትራ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለስልጣን አስታወቁ

አለም አቀፍ ህግንና የቪየና ስምምነትን በመጻረር የህወሃት የፀጥታ ሃይሎች ባሳለፍነዉ ሳምንት አንድ ኤርትራዊ ዲፕሎማትን በቦሌ አለም አቀፍ አዉሮፕላን ጣቢያ የያዟቸዉን የግል ንብረቶችና ሰነዶች በመንጠቅና በመፈተሽ ወንጀል መፈፀማቸዉን አምባሳደር ፍስሃ ፅዮን ጴጥሮስ በኤርትራ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ከፍተኛ ባለስልጣን ገለጸዋል።

ከአዲስ አበባ በካይሮ በኩል ወደ አስመራ በመሄድ ላይ የነበሩት ዲፕሎማት፣ ተገቢዉን ህጋዊ የኢሚግሬሽን ደንቦችን ያሟሉ ቢሆንም የፀጥታ ሃይሎቹ የያለመነካት የዲፕሎማቲክ መብታቸዉን በመግፈፍ እንዳንገላቷቸዉና እንዳጉሏሏቸዉ ተናግረዋል።

የዲፕሎማቱን ሻንጣ፤ ላፕ ቶፕ ኮምፒዩተር ከመፈተሽ አልፎ ተርፎ ከአንድ ሰአት ተኩል በላይ በአዉሮፕላን ጣቢያዉ በእስር እንዳቆዩዋቸዉ እኒሁ የኤርትራ መንግስት የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለስልጣን ገልፀዋል።

አዉሮፕላን እስኪሳፈሩ ድረስ የፀጥታ ሃይሎቹ በኤርትራዊዉ ዲፕሎማት ላይ ከፍተኛ ክትትል ሲያደርጉባቸዉ እንደነበር የገለፁት አምባሳደር ፍስሃፅዮን፣ የህወሃት አገዛዝ በአለም አቀፍ ህግና በቪየናዉ ስምምነት መሰረት ለተፈፀመዉ ወንጀል በህግ እንደሚጠየቅ መግለፃቸዉን አል አፍሪካን ኒዉስ የዜና አገልግሎት ገልጿል።

ህወሃቶች በጫካ ካሳለፉት ዕድሜ በላይ የተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶች መናሄሪያ በሆነቺው አድስ አበባ ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ እየኖሩ ቢሆንም የመንግሥት አስተዳደርና የህግ የበላይነት የማሳሰሉ ኢሴቶች እስከዛሬ እንዳልተዋሃዳቸው ከሚወስዱት እርምጃ መገምገም ይቻላል የሚሉ ዲፕሎማቶች ቁጥር ቀላል አይደለም። ወያኔ በዱሬ እንኳ ህግ እንደሚመራ በምርጫ 97 ቅስቀሳ ወቅት በሰፊው ሲገለጽ እንደነበር አይዘነጋም።

## መድረክ ከቅንጅት ወደ ግንባር መሸጋገሩ ተገለጸ

አዲሱ ግንባር ከጥቅምት 2 ቀን 2004 ባወጣው መግለጫ ላይ እንዳመለከተው መለስተኛ የፖለቲካ ፕሮግራሙ የግንባሩ ፕሮግራም ሆኖ እንዲያገለግል በመስማማት መድረክን እስካሁን ከነበረበት የቅንጅት አደረጃጀት ከፍ ወዳለ የግንባር አደረጃጀት ለማሸጋጋር የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወስኗል።

መድረክ በግንባሩ ዙሪያ የተሰባሰቡት የአረና ትግራይ ለፍትህና ለዲሞክርአሲ፣ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክርአሲያዊ ንቅናቄ፣ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ፣ የኢትዮጥያ ሶሻል ዲሞክርአሲያዊ ህብረት እንዲሁም አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በጋራ ለመታገል የተስማማሙባቸው የመለስተኛ ፕሮግራም መሰረታዊ መርሆዎች ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት፣ እንዲሁም ኢፍተሀዊና አድሎአዊ አሰራሮች የተወገዱበት፣ በመከባበር ላይ የተመሰረተአንድነት እንዲጠናከር መቆም፤ መገንጠልን ያለመደገፍ፣ የግለሰብ፣ የብሄረሰቦች፣ ህዝቦችና የቡድን መብቶች እኩል እንዲከበሩ፣ ሰብአዊና ዲሞክርአሲያዊ መብቶች የሚከበሩባትና ማህበረ- ኢኮኖሚ ፍትህ የሰፈነባት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት ጠንክሮ ለመንቀሳቀስ የሚሉት ይገኙበታል።

መድረክ በነጻ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ ያልተገደበ መብት ማረጋገጥ፣ የመናገር፣ የመጻፍና ሀሳብን የመግለጽ መብቶች እንዲከበሩ፣ ነጻ ፍትሀዊ ምርጫን በገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ ለማከናወንና የመድብለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታን እውን የሚሆንበት ስርአት ለመገንባት እንደሚንቀሳቀስ ገልጿል።

መድረክ አያይዞም "በመሰረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ብሄራዊ መግባባት ለመፍጠር የብሄራዊ መግባባት ውይይት እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣ በዚህም የብሄራዊ ማግባባት ውይይት ላይ አሁን በስልጣን ላይ ያለውን ገዢ ፓርቲ ጨምሮ በሀገር ውስጥና በውጭ በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱትን እና በትጥቅ ትግል አለማቸውን የሚአራምዱትን የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሰላማዊ ትግሉ ጎራ ተቀላቅለው በብሄራዊ መግባባት ውይይት ላይ እንዲሳተፉ ለማግባባት ጥረት ለማድረግና ለስልጣን ከበቃ ደግሞ ሁሉን የፖለቲካ ሀይሎች የሚያሳትፍ ብሄራዊ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መንግስት እንደሚያቋቁም ጠቅሷል።

የአገራችን ፖለቲካ ከቂም በቀልና ከጥላቻ ስሜት እንዲሁም ከተለያዩ ቁርሾዎች የሚላቀቅበት ሁኔታ እንዲፈጠር ለመታገል፣ ህገ መንግስቱ ሁሉን የፖለቲካ ድርጅቶችና ህዝቡን ባሳተፈ መልኩ ውይይት ተደርጎበት በህዝብ ውሳኔ ጭምር የሚሻሻልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ተግቶ እንደሚሰራ መድረግ አስታውቋል።

መድረክ "የህንን በኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች የህብረት ጥያቄ ላይ ወሳኝ የሆነውን እርምጃ ፣ ጉዳዩን በጉጉት ሲጠብቀው ለነበረው መላው ሀገር ወዳድ ህዝባችንና ለአለማቀፉ የኢትዮጵያ ወዳጅ ወገኖች ሁሉ ስናበስር በታላቅ ደስታ ነው" ብሎአል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የተከሰተውን የርሃብ አደጋ . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እውነታው ይህ መሆኑ እየታወቀ ዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የተከሰተውን ረሃብና እልቂት ዘጋቢዎች በትክክል እንዳይዘግቡ የሚችለውን ሁሉ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን የእራሱ የሚገዛትን አገር ችግር በመደበቅ ረሃቡ ሌሎች ከሰሃራ በታች ያሉትን አገሮች ክፉኛ እንዳጠቃ ነገር ግን ኢትዮጵያ ለረሀብ የሚያጋልጡ ችግሮችን ለመቅረፍ ችላለች በማለት ባዶ ፕሮፖጋንዳ እየነዛ እንደሆነ ታውቁአል።

ይህ በእንዲህ እያለ ካራቱሪ በመባል የሚታወቀው ኩባንያ ከዘራፊው የወያኔ አገዛዝ የተቸረለትን ለም መሬት ከህንድ አገር ለሚመጡ ገበሬዎች የማከራየት እቅድ እንዳለው አዲስ ነገር ኦን ላይን በመባል የሚታወቀው የዜና አውታር፣ አጋልጦአል። በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንን ከቀያቸው በጦር መሳሪያ በማስገደድ እያፈናቀለ ለውጪ ሃገራት ኩባንያዎች የኢትዮጵያን ለም መሬት እየቸበቸበ ያለው አጥፊው የወያኔ አገዛዝ አሁንም ለዚሁ የካራቱሪ ኩባንያ የአዲስ አበባ ከተማን ግማሽ የሚያክል 25 ሺህ ሄክታር ተጨማሪ ለም መሬት ከጋምቤላ ክልል የሸጠ መሆኑ ታውቁአል። የካራቱሪ ኩባንያ በጋምቤላ ክልል ብቻ ከ 300 ሺህ ሄክታር ለም መሬት ከዘረኛው አገዛዝ በርካሽ ዋጋ መግዛቱ ይታወሳል።

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ለማጥፋት ቆርጦ በተነሳው ዘረኛ አገዛዝ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በግፍ ከቀያቸው እየተፈናቀሉ፣ ለርሃብና ሞት እየተዳረጉ በሚገኙበት ሁኔታ የሃገሪቱን ለም መሬትና አንጡራ ሃብት ለውጪ ሃገራት ባለሃብቶች በዘፈቀደ መቸብቸቡን ለማስቆም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንዲነሳ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ጥሪ ማቅረቡ አይዘነጋም።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**፡- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**፡- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz**
**እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org